ፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ

Higher Education Relevance and Quality Agency

HERQA

ቁጥር 09/7-1/7916/09
Ref.No

ቀን 28 ጥቅምት 2009
Date

በከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም ትምህርት ለማካሄድ የተሰጠ የእዉቅና እድሳት ፈቃድ

ተቋም፡ ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርስቲ

ካምፓስ፡ ቢሾፍቱ

ተቋሙ በሰርቬይንግ ቴክኖሎጂ የትምህርት መስክ በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ትምህርት ለመስጠት እስከ ነሐሴ 2012 ዓ.ም ድረስ የእዉቅና ፍቃድ ዕድሳት ለሁለተኛ ጊዜ ተሰጥቶታል፡፡

በግምገማዉ ዉጤት መሰረት ተገቢዉን ማሻሻያ ለማድረግ እንዲረዳ ዝርዝር ሪፖርት ለተቋሙ ተልኳል፡፡

**Re-accreditation Granted to Provide a Higher Education Program**

**Institution: Rift Valley University**

**Campus: Beshoftu**

The Institution has been reaccredited to provide undergraduate program in Surveying Technology. The Re-accreditation shall be effective until August 2020.

The detail report of the assessment is delivered to the Institution for the recommended improvements.

ከሰላምታ ጋር

ታምራት ጥጋ
ምክትል ዋና ዳይሬክተር

ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
ለም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
ለዕ/ኢ/ሊ/ግ እና የት/ማ/ማ ዳይሬክተር
ለህዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ
ከትአጥኤ

የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ

Higher Education Relevance and Quality Agency

ቁጥር / Ref.No 09/7-1/7822/09

ቀን / Date 11 8 ጥቅምት 2009

## በከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም ትምህርት ለማካሄድ የተሰጠ የእዉቅና ፈቃድ

## Accreditation Granted to Provide a Higher Education Program

ተቋም: ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ

ካምፓስ: ቢሾፍቱ

ቋሙ በመደበኛው መርሀ ግብር በቅድመ ምረቃ ደረጃ በቢዝነስ ጅመንት እስከ ነሐሴ 2012 እና በነርሲንግ የትምህርት መስክ እስከ ነሐሴ 2013 ዓ.ም ድረስ ትምህርት እንዲሰጥ የእዉቅና ፍቃድ እድሳት ለሁለተኛ ጊዜ ታድሷል።

በግምገማዉ ውጤት መሰረት ተገቢውን ማሻሻያ ለማድረግ እንዲረዳ ዝርዝር ሪፖርት ለተቋሙ ተልኳል።

Institution: Rift Valley University

Campus: Bishoftu

The Institution has been reaccredited for the 2rd time to provide education in *Business Management* and *Nursing* at undergraduate level in a regular modality.

The reaccreditation will be effective until August 2020 and August 2021 to Business Management and Nursing respectively.

The detail evaluation report is delivered to the institution for the recommended improvements.

ታምራት ጭታ

ምክትል ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፤

ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት

ለም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት

ለእ/አ/አ/ግ እና የት/ማ/ማ ዳይሬክቶሬት

ለህዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ

ከትአጥኤ

HERQA

ቁጥር 09/7-1/782/11
Ref.No
ቀን 22 ግንቦት 2011
Date

## በከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም ስልጠና ለማካሄድ የተሰጠ የእውቅና ፈቃድ

## Accreditation Granted to Provide a Higher Education Program

ተቋም፡- ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርስቲ
ካ ስ፡- ቢሾፍቱ

ተቋሙ በአካውንቲንግ ኤንድ ፋይናንስ የትምህርት መስክ በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ በመደበኛው መርሐ-ግብር በየዓመቱ ከ50 የማይበልጡ ተማሪዎችን እየተቀበለ ስልጠናውን እንዲቀጥል እስከ መስከረም 2016 ዓ.ም የዕውቅና ፈቃዱ ታድሶለታል፡፡

ግምገማው ውጤት መሰረት ተገቢውን ማሻሻያ ማድረግ እንዲረዳው የግምገማው ዝርዝር ሪፖርት ተቋሙ ተልኳል፡፡

ታ ጋር

ታምራት ሞታ
ምክትል ዳይሬክተር

**Institution:-** Rift Valley University

**Campus:-** Bishoftu

The Institution has been re accredited to provide higher education in Accounting and Finance program at undergraduate level in regular modality with annual intake of 50 students. The reaccreditation shall be effective until September 2023.

The detail report of the assessment is delivered to the institution for the recommended improvements.

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia Higher Education Relevance & Quality Agency

ግልባጭ፡

ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
ለም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
ለእ/አ/አ/ግ እና የት/ማ/ማ ዳይሬክቶሬት
ለህዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ
ከትአጥኤ

የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ

HERQA

Higher Education Relevance and Quality Agency

ቁጥር / Ref.No 09/7-1/7822/09

ቀን / Date 18 ጥቅምት 2009

## በከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም ትምህርት ለማካሄድ የተሰጠ የእዉቅና ፈቃድ

ተቋም: ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ

ካምፓስ: ቢሾፍቱ

ቋሙ በመደበኛው መርሀ ግብር በቅድመ ምረቃ ደረጃ በቢዝነስ ጅመንት እስከ ነሐሴ 2012 እና በነርሲንግ የትምህርት መስክ እስከ ነሐሴ 2013 ዓ.ም ድረስ ትምህርት እንዲሰጥ የእዉቅና ፍቃድ እድሳት ለሁለተኛ ጊዜ ታድሷል።

በግምገማዉ ውጤት መሰረት ተገቢውን ማሻሻያ ለማድረግ እንዲረዳ ዝርዝር ሪፖርት ለተቋሙ ተልኳል።

## Accreditation Granted to Provide a Higher Education Program

**Institution:** Rift Valley University

**Campus:** Bishoftu

The Institution has been reaccredited for the 2nd time to provide education in *Business Management* and *Nursing* at undergraduate level in a regular modality.

The reaccreditation will be effective until August 2020 and August 2021 to Business Management and Nursing respectively.

The detail evaluation report is delivered to the institution for the recommended improvements.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Higher Education Relevance & Quality Agency

ታምራት ጥታ
ምክትል ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፤

ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት

ለም/ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት

ለአ/አ/አ/ግ እና የት/ማ/ማ ዳይሬክቶሬት

ለህዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ

ከትአጥኤ

# የእዉቅና ፈቃድ ዕድሳት ግምገማ ማጠቃለያ ሪፖርት

I. አጠቃላይ መረጃ

1 የተቋሙ ስም፡ ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ

2 ካምፓስ፡ ቢሾፍቱ

3 አድራሻ፡ ካምፓሱ የሚገኝበት ክልል ቢሾፍቱ ከተማ፡ ቢሾፍቱ

4 የስልጠና መስክ፡ ቢዝነስ ማኔጅመንት እና ነርሲንግ

5 ስልጠናዉ የሚሰጥበት ደረጃ፡ የመጀመሪያ ዲግሪ

6 ስልጠናዉ የሚሰጥበት አግባብ/ዘዴ/፡ መደበኛ

II. በዝግጅቱ ላይ የተደረገ የግምገማ ማጠቃለያ

1. **ትምህርቱ ወይም ስልጠናው የሚሰጥበት ህንፃና ከባቢያዊ ሁኔታ**

ተቋሙ የእውቅና ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ ያቀረበው ከዚህ ቀደም የእውቅና ፈቃድ ጥያቄ አቅርቦ ፈቃድ ባገኘበት ሕንፃ ውስጥ ነው። ተቋሙ ከዋናው መንገድ ዳር ያለ በመሆኑ የድምጽ ብክለት ሊኖር እንደሚችል እና ይህንን ሁኔታ ሊያርም የሚችሉ ስራዎችን መስራት ይገባዋል።

2. **አካዳሚያዊ አመራርና አደረጃጀት**

የተቋሙ አደረጃጀት የእውቅና ፈቃድ በጠየቀባቸው የትምህርት መስኮች ትምህርት ለማስቀጠል በሚያስችል ሁኔታ ላይ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

3. ተቋማዊ ሰነዶች

ተቋሙ የመማር ማስተማር፣ የምርምር እና የማሕበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉትን አሰራር የዘረጋ መሆኑን እና ይህንንም ዓላማ ለማሳካት ይረዳው ዘንድ የተለያዩ መመሪያዎችን እና ፖሊሲዎችን አዘጋጅቶ ለኤጀንሲው ያቀረበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

4. የመምህራን ፕሮፋይል

መምህራንን በተመለከተ በተቋሙ በቋሚነት የተቀጠሩ መምህራን ብዛትና ስብጥር ለየስልጠና መስኩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

Federal Democratic Republic Of Ethiopia
Higher Education Relevance & Quality Agency

| ተ.ቁ | የስልጠና መስክ | ፒኤች.ዲ | ማስተርስ | ባችለር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቢዝነስ ማኔጅመንት | - | 5 | 1 |
| 2 | ነርሲንግ | - | 4 | 1 |

ይህ የመምህራን ቁጥርና ስብጥር የእውቅና ፈቃድ ዕድሳት ለጠየቀባቸው የትምህርት መስኮች ስልጠናውን ለመቀጠል ያስችላል።

5. ስርዓተ ትምህርት

የዕውቅና ፈቃድ ለጠየቀባቸው የትምህርት መስኮች የተዘጋጁት ሥርዐተ-ትምህርቶች ከባለሙያዎች በተሰጠው አስተያየት መሰረት ማሻሻያ የተደረገባቸውና ለደረጃው የሚመጥኑ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

6. የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች እና የመምህራን ቢሮዎች

ምንም እንኳ የበለጠ መሻሻል የሚገባው ቢሆንም ለትምህርት ክፍል ሃላፊዎች እና ለመምህራን የሚሆኑ ቢሮዎችን በተገቢው ቁሳቁስ የተደራጁ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

7. የመማሪያ ክፍሎች

የመማርያ ክፍሎች የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ ለቀረበባቸው የትምህርት መስኮች በቁጥር በቂ መሆናቸውን ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን እነዚህ የመማሪያ ክፍሎች እያንዳንዳቸው በአማካይ 55 ተማሪዎችን ለማስተናገድ እንደሚችሉ እና ለመማር ማስተማር ምቹ መሆናቸውን ለመመልከት ተችሏል።

8. ቤተ-መፃህፍት እና የቤተ-መፃህፍት ግብዓቶች

ቤተ መፃህፍቱ በአንድ ጊዜ የተቋሙን 25% ተማሪዎች ማስተናገድ የሚችል ሲሆን በውስጡ የእውቅና ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ ለጠየቀባቸው የትምህርት መስኮች ትምህርት ማስቀጠል የሚያስችል የመፃህፍት ክምችት እንዳለው ለማረጋገጥ ተችሏል። ይሁን እንጂ በተቋሙ ቤተመፃህፍት ያለው የመፃህፍት ቁጥር ከፍ ሊል እንደሚገባው ለመገንዘብ ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ ተቋሙ ጆርናሎችን፣ ኢንሳይክሎፒዲያ እና ዲክሽኔሪዎችን በቤተ መፃህፍቱ እንዲኖሩ ማድረግ እንደሚገባው ለመመልከት ተችሏል።

Federal Democratic Republic Of Ethiopia Higher Education Relevance & Quality Agency

9. የኮምፒውተር ማዕከሎች

ሁለት የኮምፒውተር ቤተሙከራዎች ያሉት መሆኑን እና እያንዳንዳቸው በአንድ ጊዜ 20 ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚችሉ ሲሆን ኮምፒውተሮቹም ኔትዎርክድ ናቸው። በኮምፒውተር ቤተሙከራው የብሮድ ባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት ያለው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

10. የዲሞንስትሬሽን ክፍሎች

ተቋሙ ያዘጋጃቸው የዲሞንስተሬሽን ክፍሎች በነርሲንግ የትምህርት መስክ ትምህርት ማስቀጠል የሚያስችል መሆኑን ነገር ግን በውስጡ ያሉት ቁሳቁሶች ለመማር ማስተማር ምቹ በሚሆን መልኩ መደራጀት እንደሚገባቸው ለማረጋጥ ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ ለተግባር ትምህርት እንዲረዳው በአቅራቢያው ካሉ የጤና ተቋማት አብሮ ለመስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ሰነድ የተፈራረመ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል።

11. ጥናትና ምርምር

የጥናትና ምርምር ቢሮን የሚመራ የሰው ሃይል የተመደበለት ሲሆን ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖረው የሚያስችለውን ፖሊሲ ያዘጋጀ መሆኑን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በየዓመቱ የሪሰርች ኮንፍረንስ የሚካሄድ መሆኑን ከተደረገው ገለፃ እና ከቀረቡ ሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል።

12. የማህበረሰብ አገልግሎት

ተቋሙ በተለያየ መልኩ የማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ከተደረገው ገላፃ መረዳት ቢቻልም በቀጣይ በጥናት ላይ የተመሰረተ የማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን አሰራረ መዘርጋት ይኖርበታል።

13. የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት

ተቋሙ ራሱን የቻል የሰው ሃይል የተመደበለት የጥራት ማረጋገጫ ቢሮ ያለው ሲሆን ዓመታዊ እቅድ ተዘጋጅቶ በዚያው መሰረት ስራዎች እየተሰሩ እንዳልሆነ ግንዛቤ ተወስዷል።

14. የተደረጉ ማሻሻያዎች

ተቋሙ የአፈጻጸም ግምገማ በማከናወን ለኤጀንሲው ሪፖርት ያደረገ መሆኑን በማመልከቻ ወቅት ከቀረበው ሰነድ ለመመልከት ተችሏል። በእውቅና ፈቃድ ወቅት እንዲያሻሽል ከተገለጸለት ጉዳዮች መካከል የመፃህፍት ክምችቱን እና

የመምህራንን ቁጥርና ስብጥር በማሳደግ ረገድ አመርቂ ስራዎችን የሰራ እንደሆነ ከመስክ ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል። ሆኖም ግን ለጥናትና ምርምር የሚረዱ የአገር ውስጥ እና የውጭ ጆርናሎችን በማሰባሰብ ረገድ እና የጥራት የማስጠበቂያ ክፍሉን በማደራጀት ረገድ የሚጠበቅበትን ያህል እንዳልሆነ ለመገንዘብ ተችሏል።

15. ማጠቃለያ

ተቋሙ የዕውቅና ፈቃድ እድሳት በጠየቀባቸው የትምህርት መስኮች ስልጠናውን ማስቀጠል የሚያስችለውን ለደረጃው የተቀመጠውን አነስተኛ መስፈርት የሚያሟላ በመሆኑ በቢዝነስ ማኔጅመንት እስከ ነሐሴ 2012 እና በነርሲንግ እስከ ነሐሴ 2013 ዓ.ም ድረስ በየዓመቱ ከ55 ያልበለጡ መደበኛ ተማሪዎችን እየመዘገበ እንዲያስተምር የእውቅና ፈቃዱን ማደሱ አግባብነት ይኖረዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ተቋሙ ለሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት ማሻሻያ በማድረግ ለኤጀንሲው ማስታወቅ ይኖርበታል።

## ሊሻሻሉ የሚገቡ ጉዳዮች

- ቤተመፃህፍቱ ከስልጠናው ጋር ተዛማጅነት ባላቸው እና የቅርብ ጊዜ መፃህፍት በበለጠ እንዲደራጅ፣
- የመምህራን ቢሮዎች አሁን ካሉበት ሁኔታ በበለጠ እንዲደራጁ ተደርጎ አፈፃጸሙ ለኤጀንሲው በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ሪፖርት እንዲደረግ፣
- በተቋሙ ቤተመፃህፍት ያሉትን የመፃህፍት ቁጥር በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከፍ በማድረግ ውጤቱ ለኤጀንሲው እንዲገለጽ እንዲደረግ፣
- የዲሞንስትሬሽን ክፍሎችን ለአጠቃቀም በተመቸ መልኩ በማደራጀት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው ሪፖርት እንዲደረግ፣
- የጥናትና ምርምር ቢሮ በአስፈላጊው የሰው ሃይል እና በጀት ተደራጅቶ አፈጻጸሙ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው ሪፖርት እንዲያደርግ እና
- የመምህራን ልማት ላይ ስራዎችን በመስራት የተገኙ ውጤቶችን በየዓመቱ ለኤጀንሲው ሪፖርት እንዲያደርግ የሚሉት ናቸው።

Federal Democratic Republic Of Ethiopia Higher Education Relevance & Quality Agency